# ሁለተኛ ክፍል ሂሳብ ለ ሶስተኛ ክፍል

# ልኬት

- **<u>ርዝመትን</u>** ለምለካት ሳንቲሜተር ሜትር እና ኪሎሜትር እንጠቀማለን
- የርዝመት መለኪያዎች እርስ በ እርስ ትስስርና ዝምድና አላቸው

1ኪሎ ሜትር=1000ሜትር

1ሜትር=100ሳንቲሜትር

1ሳንቲሜትር=10ሚሊሜትር

ርዝመትን ስንደምርም ይሁን ስንቅንስ መልኪያቸው አንድ አይነት ካልሆነ መደመርም ይሁን መቀነስ አይቻልም

**<u>ለምሳሌ</u>** 8ሜትር+4ሜትር=12ሜትር

8ሜትር+4ሳንቲሜትር=አይቻልም

**<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ</u>**

1. 10ሳ.ሜ+15ሳ.ሜ=_____
2. 1ሜ+9ሜ=________
3. 10ኪ..ሜ+5ኪ..ሜ=______

4) 75ሜ+10ሜ=__________

- ርዝመትን በሜትር እንደምንለካው ሁሉ ይዘትን በ ሊትር እንልካለን
- ክብደትን ደግሞ በ ኪሎግራም እና በግራም እንለካለን

1ኪሎግራም=1000ግራም

- ልክ እንደ ርዝመት ሁሉ ክብደትም ላይ መለኪያዎቹ አንድ አይነት ሳይሆኑ መደመርም ይሁን መቀነስ አይቻልም።

**ክፍልፋዮች**

- ክፍልፋይ ማለት የተሰጠንን ቁጥር ወደ ተሰጠን ቁጥር መከፋፈል ነው።
- **ግማሽ(1/2)** ግማሽ ማለት ቁጥሩን ለ ሁለት ማካፈል ማለት ነው።

**ለምሳሌ** የ8 ግማሽ 4 ነው(8=4)

የ6ግማሽ3 ነው(6=3)

ቨ **የሚከተሉትን ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ**

1. 14=________
2. 10=________
3. 16=________
4. 18=________

- **ሩብ(1/4)** ሩብ ማለት ቁጥሩን ለ 4 ማካፈል ማለት ነው።

**ለምሳሌ**; የ12 ሩብ 3 ነው(124=3)

የ8 ሩብ 2 ነው(84=2)

**የሚከተሉትን ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ**

1. 20=______
2. 16=_______
3. 24=________
4. 32=________

- **ሲሶ** ቁጥሩን ለ 3 ማካፈል ነው ።

**ለምሳሌ;**የ 9 ሲሶ 3 ነው (9**3=3**)

የ15ሲሶ5ነው(15**3=5)**

**የሚከተሉትን ቁጥሮች ሲሶ ፈልጉ**

1. 21=_________
2. 18=_________
3. 12=_________
4. 24=_________

- ክፍልፋዮች እና ስያሜዎቻቸው

½=ግማሽ

1/3=ሲሶ

¼= ሩብ

1/5=አምሾ

1/10=አስራት

**<u>የ100 ብዜቶች</u>**

- ማንኛውም ቁጥር በ 100 ተባዛ ማለት ከተባዢው ቁጥር ጀርባ ሁለት ዜሮ መጨመር ማለት ነው።

**<u>ለምሳሌ</u>**; 6=600

4100=400

**<u>የሚከተሉትን ቁጥሮች በ 100 አባዙ</u>**

1. **8=_______**
2. **10=_______**
3. **2=_______**
4. **15=_______**
5. **234=_______**

# ነጥቦች፣ቀጥታመስመሮች እና ቅርጾች

- ነጥቦች ለመስመር እና ምስል መነሻ ነው።

▪ ይህ ነጥብ ይባላል።

ይህ መስመር ይባላል።

- መስመሮች አንድ ላይ በመጠቀም የተለያዩ ምስሎችን መስራት ይቻላል።

**ለምሳሌ** ጎነ ሶስት

ጎነ አራት

ክብ

ካሬ



# ገንዘብ

- ሀገራችን 5 የሳንቲም እና 5የብር ወይም የውርቀት ገንዘቦች አሉዋት።

  **እነሱም 5 ሳንቲም**

  **10ሳንቲም**

  **25ሳንቲም**

  **50ሳንቲም**

  **1ብር**

- **የወረቀት ገንዘቦች ደሞ 5ብር**

  **10ብር**

  **50ብር**

  **100ብር**

  **200ብር**

- **የውርቀት ገንዘብ እና ሳንቲሞች እርስ በእርስ ይዛምዳሉ።**

**ለምሳሌ 1 ብር 2 50 ሳንቲም ነው**

**50 ብር ደግሞ 5 ባለ 10 ብር ወረቀት ነው።**

# ግዜ

- ግዜ የሚለካ ነገር ነው።
- የሚልካው ደግሞ በ ሰዐት ነው።
- እያንዳንዱ ሰአት ዉስጥ ደግሞ ደቂቃዎች አሉት።

| ቁጥር | ደቂቃ |
|---|---|
| 1 | 5 |
| 2 | 10 |
| 3 | 15 |
| 4 | 20 |
| 5 | 25 |
| 6 | 30 |
| 7 | 35 |
| 8 | 40 |
| 9 | 45 |
| 10 | 50 |
| 11 | 55 |
| 12 | 60 |